# የገንዘብ ሚኒስቴር

## አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ማሻሻያ

**መመሪያ ቁጥር 894/2014**

የገንዘብ ሚኒስቴር

**ግንቦት 2014 ዓ.ም**



Disebled Dir.Was/GT

# መመሪያ ቁጥር 894/2014

## አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ማሻሻያ

**1. አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**2 ማሻሻያ**

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 230/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀጽ 5 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 5 ተተክቷል፡፡

“**5. ተሽከርካሪ ከቀረጥ ታክስ ነፃ ስለማስገባት**

የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ቅድመ - ሁኔታዎች በሙሉ አሟልቶ ሲቀርብ፣

1. የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ሆኖ ለማሽከርከር አካላዊ ችሎታ ያለው አካል ጉዳተኛ ከሆነ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሰራ አንድ ባለሁለት እግር ወንበር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ልዩ አወቶሞቢል፤

2. በአካላዊ ችግር ምክንያት የማሽከርከር ችሎታ የሌለው እና የማሽከርከር ችሎታ እንደሌለው በሐኪሞች ቦርድ እና በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ አካል ጉዳተኛ ከሆነ ለግል አገልግሎት የሚውል አንድ መደበኛ አውቶሞቢል፤

ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደአገር ማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ መግዛት ይችላል፡፡

2/ የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(1) (ሰ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6(1) (ሰ) ተተክቷል፡፡

“6(1) (ሰ). በተሽከርካሪው ለመገልገል የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ያለው መሆኑን ከሚከተሉት አማራጮች በአንዱ ማረጋገጥ አለበት፤

1. የመብቱ ተጠቃሚ ተቀጣሪ ሰራተኛ ወይም በጡረታ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት



Disebled Dir.Was/GT

ቀን በፊት ባሉት ሁለት አመታት የተከፈለው ከግብር በኋላ የተጣራ ደመወዝ ወይም የጡረታ አበል ለባለሁለት እና ለባለሦስት እግር የሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ቢያንስ ብር 60,000 (ስልሳ ሺህ ብር) እና ለመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን ቢያንስ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆን ያለበት ሲሆን፣ ከቀጣሪው አካል የደመወዙን ልክና በዚህ ደመወዙ ላይ ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የጡረታ አበል መቀበያ ደብተር ማቅረብ አለበት፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በግል ገቢ በሚያስገኝ ወይም የንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ባለሁለት እና ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ለልዩ አውቶሞቢል ሲሆን፣ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢ ቢያንስ 60,000 (ስልሳ ሺህ ብር)፣ ለመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን፣ ደግሞ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡”

3/ ከመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(1)(ቸ) ቀጥሎ የሚከተለው ተራ ፊደል (ነ) ተጨምሯል፡፡

“(ነ) ተሽከርካሪው በግዥ የተገኘ ከሆነ የተገዛበትን ደረሰኝ ወይም በስጦታ የተገኘ ከሆነ ሰጪው በሚገኝበት አገር በሚገኝ ውል አዋዋይ ሹም የተረጋገጠ የስጦታ የምስክር ወረቀት እና የዕቃ ማስጫኛ ሰነድ፤”

4/ የመመሪያው አንቀጽ 6(2)(1)(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6(2)(1)(ለ) ተተክቷል፡፡

“6(2)(1)(ለ). በአካላዊ ችግር ምክንያት የመብቱ ተጠቃሚ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ወይም ከአገር ውስጥ መገጣጠሚያ ፋብሪካ የገዛውን ተሽከርካሪ የማሽከርከር ችሎታ የሌለው በመሆኑ በቤተሰብ አካል የሚያንቀሳቅሰው ከሆነ አስቀድሞ በሚመለከተው መስተዳድር የተረጋገጠ እና የቤተሰብ ዝርዝርን የያዘ ሕጋዊ ሰነድ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት፡፡”

5/ ከመመሪያው አንቀጽ 6(2)(1)(ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (መ) ተጨምሯል፡፡

“6(2)(1)(መ). የመብቱን ተጠቃሚ ስም፣ አድራሻ ፤ ፎቶግራፍ እንዲሁም በሕክምና ተቋም የተረጋገጠውን የአካል ጉዳቱን ዓይነት እና መጠን የሚያሳይ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የመታወቂያ ወረቀት በማናቸውም ጊዜ በተሽከርካሪው ውስጥ እንዲኖር ማድረግ እና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፡፡”

**3. <u>ማሻሻያው የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል

*አዲስ አበባ ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*